# ወቅታዊ የኩፍኝ ወረርሽኝ ተከስቷል

## ኩፍኝ እየተስፋፋ ነው።

**ኩፍኝ በቫይረስ የሚመጣ በጣም ተላላፊ በሽታ ነው። በተለይም ለህጻናት እና ለትናንሽ ልጆች፣ አደገኛ ሊሆን ይችላል። ቤተሰብዎን እና ማህበረሰብዎን ይጠብቁ።**



**የታመመ ሰው ሲያስል ወይም ሲያስነጥስ ኩፍኝ በአየር ይተላለፋል።** የኩፍኝ በሽታ ያለበት ሰው ቦታውን ከለቀቀ በኋላ ቫይረሱ ለ 2 ሰዓታት በአየር ውስጥ ሊቆይ ይችላል። በጣም ተላላፊ ከመሆኑ የተነሳ ከ 10 ሰዎች ውስጥ 9 ያህሉ ኩፍኝ ወዳለበት ሰው አጠገብ ከሚመጡ እና በክትባት ያልተጠበቁ ሰዎችም ይያዛሉ።

**የኩፍኝ ምልክቶች ከቫይረሱ ጋር ከተገናኙ በኋላ ከ 7 እስከ 14 ቀናት ውስጥ ይታያሉ። የተለመዱ የኩፍኝ ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦**



**ከፍተኛ ትኩሳት**
(ከ 104°F በላይ ሊጨምር የሚችል)



**ሳል**



**የአፍንጫ ንፍጥ**



**ቀይ እና/ወይም ውሃማ አይኖች**



**ሽፍታ**
(ምልክቶች ከታዩ ከ3-5 ቀናት በኋላ ይከሰታል)

**ኩፍኝ የሚከተሉትን ጨምሮ፣ ከባድ የጤና ችግሮች ሊያስከትል ይችላል፦**



**የሳንባ ምች (ኒሞኒያ)**



**የአንጎል እብጠት**
(ኢንሰፍላይትስ)



**ሞትም ልያጋጥም ይችላል**



## ከኩፍኝ በሽታ ለመከላከል በጣም ጥሩው መንገድ...

የኩፍኝ፣ የደግፍ እና የሩቤላ በሽታ (MMR) ክትባት ነው። ለመከተብ በጣም አልዘገዩም። ክትባት እርስዎን፣ በዙሪያዎ ያሉትን ሰዎች እና ማህበረሰብዎን ለመጠበቅ ይረዳል። ያልተከተቡ ከሆነ፣ በአካባቢው ያለው የኩፍኝ በሽታ እስኪቀንስ ድረስ ቤት ውስጥ ወይም ከተጨናነቁ አካባቢዎች መራቅን ያስቡበት፣ በተለይም ከቤተሰብዎ ውስጥ በጣም ሊታመሙ የሚችሉ ሰዎችን ለመጠበቅ።

**እርስዎ ወይም ከቤተሰብዎ ውስጥ ያለ ሰው ኩፍኝ እንዳለብዎ ካሰቡ፣ ከሌሎች ይራቁ እና የጤና እንክብካቤ አቅራቢን፣ አስቸኳይ እንክብካቤን ወይም የድንገተኛ ክፍልን ይደውሉ።**